ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

እሮብ ግንቦት 20 2000 ዓ.ም

## በዋሽንግተን ዲ.ሲ ከተማ ሲድስ የሚባል ድርጅት ለእነ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይሳቅ ሽልማት ሰጠ። ድርጊቱ አሳፋሪና ሊያስወቅስ የሚገባው ነው ተባለ።

እሁድ ግንቦት 17 2000 በዋሽንግተን ዲ.ሲ ከተማ ሲድስ በሚባል ለኢትዮጵያ ሰላም፤እውቀት፤ኢኮኖሚና ባህል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉ ሰዎችና ድርጅቶች ሽልማት የሚሰጥ ድርጅት የአመቱን ሽልማቱን የሰጠበት ዝግጅት ነበር። ከተሸላሚዎቹ ውስጥ አንዱ የሆነው “የተባበሩት የአገር ሽማግሌዎች ለሰላም ብሄራዊ ኮሚቴ” በሚል ስም ራሱን ያዋቀረውና በአገሪቱ ሰላም በማምጣት ስም በተለይም ደግሞ ‹የቅንጅት መሪዎችን ለማስፈታት የአስታራቂነትና የሽምግልና ስራ በመስራቱ› የተሸለመው በፕሮፌሰር ኤፍሬም የሚመራው ይህ የሽማግሌዎች ቡድን ነበር። ይህ ሽልማት የሚሰጠው ላለፈው ስራቸው ለማመስገንና ወደፊትም ይህንን ስራ እንዲቀጥሉበት ለማበረታታት መሆኑ ነው። ይህ መቼም በአካባቢው የነበሩትን ብዙ ኢትዮጵያውያን በተለይም በአካባቢው ያሉና ከእስር የተለቀቁትን የቅንጅት አመራሮች በጣም ያስገረመና ያሳዘነ ድርጊት የሻላሚ ድርጅቱን ነፃነትና ይዞ የሚንቀሳቀሰውን እሴት ትክክለኛነት ከፍተኛ ጥያቄ ውስጥ የከተተ ድርጊት ነበር። ይህ የተደረገው ደግሞ ከእስረኞቹ ውስጥ አንዱ የዚህን ሽልማት ፍፁም አግባብ አለመሆን ለአዘጋጆቹም ከተነገራቸው በሁዋላ ነው።

ይህ የተሸለመ የሽማግሌዎች ቡድን በምንም ሂሳብ (ፍላጎቱ ምንም ሆነ ምን) የቅንጅት መሪዎችን ጉዳይ የያዘበት አካሄድ ለኢትዮጵያ ሰላምን ያመጣ ወይንም የሚያመጣ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን በአገራችን ከሽማግሌዎች የሚጠበቀውን ገለልተኛነትና ክብር ያልሰጠ፤ እንዲያውም የሽምግልናን ክብር ያዋረደ፤ በፕሮፌሰር ኤፍሬም በኩል በቀጥታ የአቶ መለስና የመንግስታቸው አሳፋሪ የውሸትና የማጭበርበር መሳሪያ የሆነ መሆኑንና ለዚህም በተለይ ተጠያቂ የሆነው ፕሮፌሰር ኤፍሬም መሆኑን በጊዜው በውይይቱ ላይ የነበሩ ሁሉ የሚያውቁት ነው። ይህ ቡድንና በተለይም ፕሮፌሰር ኤፍሬም ወደፊትም ምንም አይነት ቁም ነገር ያለው የሽምግልና ስራ ሊሰራ የማይችልና የማይገባው መሆኑም ከተጠቀመው የእነመለስ መንግስት በቀር ማንም ለራሱ ክብር ያለው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት የሚያውቀው ነው። ለዚህም ነው በቅንጅት ጉዳይ ከታየው አሳፋሪ ድርጊት በሁዋላ እነፕሮፌሰር ኤፍሬም ‹በሽምግልና ስም› የቀረቡዋቸው ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ፊት የነሱዋቸው። ይህ ቡድን በሽምግልና ስም ሊሸለም ቀርቶ እራሱ ሽምግልና የሚለውን ባህላዊ ተቁዋም ያዋረደ ድርጅት ነው።

ይህንን ቡድን በኢትዮጵያውያን ስም መሸለም በእርግጥም በጣም የሚያሳፍርና ሸላሚውንም ድርጅት ከፍተኛ ትዝብት ውስጥ የሚጥል መሆኑን የዝግጅት ክፍላችን ያሳውቃል።